የአማራ ፖለቲካ

ከዚህ ወዴት? እንዴት?



መስከረም 2012

የአማራ ፖለቲካ
ከዚህ ወዴት? እንዴት?

መስከረም 2012 ዓ.ም

ማውጫ

1. መግቢያ 4

2. ያለንበት ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ 7

2.1. የመጠቅለል ፖለቲካ እና መዘዙ 7

2.2. የሕወሓት ቀጣይ የጥፋት እርምጃዎች 9

2.3. የፖለቲካ ሽግግር 10

2.4. የብሉይ ዘመን ድህነት እና የደቀነው አደጋ 13

2.5. ‹ኦሊጋርኪ› የደቀነው ፈተና 13

3. ምንይሻለል? 15

3.1. የፉክክር ሳይሆን የትብብር ዘመን መሆኑን መገንዘብ 15

3.2. አማራነትና ኢትዮጵያዊነት 19

3.3. የጠማሪያኑ ሚና 20

3.4. የሕዝብግንኙነት ቀውስ 22

3.5. የቆምንላቸው መሠረታዊ መርሆዎች 24

3.6. የትግል ቅደምተከተል 26

3.7. የኬራላአብነት 31

3.8. የአማራብሔርተኝነትንማጽናት 34

1. መግቢያ

ትልቅ ፈተና ላይ ነን:: ይህ ጊዜ የአማራ ሕዝብ የፈተና ጊዜ ነው:: ዛሬም እንደ ትናንቱ በራሳችን የውስጥ ችግር ምክንያት ለከባድ ሽንፈት ተዳርገናል:: ታሪካችንን በደንብ የመረመረ ሰው እንደሚገነዘበው፣ የአማራ ሕዝብ የጠላቶቹ ሰለባ ሲሆን የኖረው በወደረኞቹ ጥንካሬ ሳይሆን በውስጡ በሚፈጠሩ ሽኩቻዎችና መቋሰሎች ምክንያት ነው:: በአማራ ሕዝብ ላይ የደረሱትና እየደረሱ ያሉት አደጋዎች በአመዛኙ ከውጭ የሚመጡ አይደሉም:: አርቆ ማሰብ እየተሳነን በጊዜያዊ የሥልጣንና የጥቅም ግጭት ስንራኮት የጠላት መጫዎቻ እንሆናለን:: ለሁላችንም የሚበቃ ነገር መገንባት እየቻልን ባለችው ኩርማን ላይ ስንራኮት የተኩላዎች መጫዎቻ ስንሆን ኖረናል፤ ከትናንት እስከዛሬ::

የአማራ ልጆች ይህ ወቅት አሳፋሪ በሆነ ሽንፈት ውስጥ የምንገኝበት ወቅት መሆኑን መቀበል ይገባናል:: እየመረረንም ቢሆን ሐቁን እንቀበል:: ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም. በአማራ ክልል የተፈጠረው ክስተት ትልቅ ሽንፈት ውስጥ ከትቶናል:: ይህን በራሳችን የውስጥ ችግር ምክንያት የተፈጠረ አደጋ አቃለን ካየነው ውድ ዋጋ እንከፍልበታለን:: ያለ ጥርጥር የሰኔ 15ን ጉዳይ በጥንቃቄና በአርቆ አሳቢነት ካልተሻገርነው በሁሉም ቤትና ድርጅት ውስጥ እየገባ አማራዊ ጎብረታችንን ማወኩን ይቀጥላል:: ሰኔ 15 የፈጠረው ቁስል እያመረቀዘ አዴፓን፣ አብንን፣ አድማስን፣ አሥራትን እና ሌሎች በውጭና በሀገር ቤት የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካና ሲቪክ ድርጅቶቻችንን መበጥበጡን ይቀጥላል:: ወደረኞቻችንም ዛሬም እንደ ትናንቱ በውስጣችን በሚፈጠሩ ልዩነቶች እየገቡ ልዩነቶችን በማስፋት ሕዝባችንን ለማዳከም የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም::[1]

ያለን ምርጫ ግልጽና አጭር ነው:: መፍትሔው ሰኔ 15ን እንዳልተፈጠረ ለመርሳት መሞከር አይደለም:: መፍትሔው ክስተቱን ሸፋፍኖ ማለፍም በጭራሽ ሊሆን አይችልም:: መፍትሔው ችግሩንና የችግሩን ምንጭ ወደ ውጪ መግፋትም አይደለም:: መፍትሔው አሁን የማኅበራዊ ሚዲያ ጦማሪያኑ ኀላፊነት በጎደለው መልኩ እንደሚያደርጉት ማዶና ማዶ ሆኖ መጨፋጨፍም አይደለም:: መፍትሔው ሐቁን መቀበል ነው:: አደጋው የተከሰተው በውስጣችን በተፈጠረ ሽኩቻና ልዩነት ምክንያት መሆኑን፣ ይህን በውስጣችን

[1] *ያለን ምርጫ አንድም ውስጣዊ አንድነታችንን አጠንክረን እና በሸንፈት ዘመን "አንሸነፍም!" ብለን መነሳት፣ አለያም ከሐቅ ጋር ተጣልተንና አማራዊ ጎብረታችንና አንድነታችንን አዳክመን ራሳችንን ለጠላት አሳልፈን መስጠት ነው::*

የተፈጠረ አላስፈላጊ ልዩነት ወደረኞቻችን በሚገባ እንደተጠቀሙበትና እየተጠቀሙበት እንደሆነ ማወቅ[2] እና ችግሩ ሕዝባችንን በሚጠግን መልኩ ሊፈታ የሚችለውም ሐቁን ተቀብለን በአማራ ነባር ዕሴት መሠረት በሽምግልናና በእርቅ ስንቋጨው መሆኑን በሚገባ መገንዘብ ይገባናል::[3]

ግልጽ መሆን ያለበት፣ የተሸነፍነው አንድ አውደ ውጊያ (battle) እንጅ ጦርነቱን አይደለም:: አሁን ባለንበት ቁመና፣ እንደተዝረከረክን በመሳከር ውስጥ የምንቀጥል ከሆነ ግን ጦርነቱንም መሸነፋችን አይቀርም:: ያ እንዳይሆን የሰኔ 15ቱ አደጋ እንዴት ተፈጠረ? ለምን ተፈጠረ? ተጨማሪ አደጋዎች እንዳይፈጠሩና ሕዝባችን ለዳግም ሽንፈት እንዳይዳረግ ምን ቢደረግ ይሻላል? በሚሉት ነጥቦች ላይ አበክረን መወያየት ይገባናል::

የዚህች አነስተኛ ጽሑፍ ዓላማ ይህ ነው፤ ውይይትን መጋበዝ:: እንወያይ! መላ እንምታ! የሚያድነን የሰከነና የሰለጠነ ውይይት ብቻ ነው:: ከተራ ጩኸትና አሉባልታ ወጥተን በዕውቀት (መረጃና ማስረጃ) ላይ የተመሠረተ የውይይት ባህል ልንገነባ ይገባል::

---

[2] አደጋው ከተከሰተ ማግስት ጀምሮ ከክስተቱ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላቸው በጣም በርካታ ንጹሐን የአማራ ልጆች በገፍ ታስረው እንደተሰቃዩና እየተሰቃዩ እንደሚገኙ በግልጽ ይታወቃል::

[3] ሁልጊዜም የአማራ ጠላቶች ሕዝባችንን የሚያደሙት የውስጣችንን ልዩነት እየተጠቀሙ ነው:: አሁንም ወደረኞቻችን አንዱን ገዳይ ሌላውን ተገዳይ በማድረግና ደረጃ በመመደብ አንዱ አማራ በሌላው አማራ ላይ እንዲነሳ እና ሁለተኛ ሞት እንድንሞት አበክረው እየሠሩ ነው:: ብዙ የዋሕ ወገኖችም "አያ በሬ ሳሩን እየሀና ገደሉን ሳታይ..." እንደሚባለው ወደረኞቻችን ባዘጋጁልን ወጥመድ ውስጥ ዘው ብለው ገብተው ሲዳክሩ እየታዘብን ነው::

አርቆ ማሰብ እየተሳነን በጊዜያዊ የሥልጣንና የጥቅም ግጭት ስንራኮት የጠላት መጫዎቻ እንሆናለን። ለሁላችንም የሚበቃ ነገር መገንባት እየቻልን ባለችው ኩርማን ላይ ስንራኮት የተኩላዎች መጫዎቻ ስንሆን ኖረናል፤ ከትናንት እስከ ዛሬ።

2. ያለንበት ወቅታዊ የፖለቲካ ሁኔታ

2.1.የመጠቅለል ፖለቲካ እና መዘዙ

በአንድ ሀገር ሕዝቦች መካከል የዘውግ፣ የሃይማኖት፣ የመደብ ወይም የሌላ ማንኛውም ዓይነት ልዩነት መኖር በራሱ ችግር አይደለም:: ልዩነት የግጭት ምንጭ የሚሆነው ከድህነት ጋር የተገናኘ እንደሆነ ነው፤ ልዩነት ትልቅ አደጋ የሚፈጥረው የእኩልነት፣ ፍትሕና ዴሞክራሲ እጦት ሲኖር ነው:: በሀገራችን የሚታየው ነባራዊ ሐቅ ይህን የሚያሳይ ነው:: በየቦታው የሚታዩት ግጭቶችና የሕዝብ መፈናቀሎች ከድህነት ጋር በእጅጉ የተቆራኙ ናቸው፤ ከእኩልነት ይልቅ አግላይ (exclusionary) የሆነ፣ ከፍትሕ ይልቅ ኢፍትሐዊና ኢዴሞክራሲያዊ የሆነ የፖለቲካ ሁኔታ በመኖሩ የተፈጠሩ ናቸው::[4]

ሕወሓት በእኩልነትና ፍትሐዊነት ስም እየማለ እና እየተገዘተ፣ ነገር ግን በተግባር ምን ያህል ፀረ እኩልነትና ፀረ ፍትሕ እንደነበር በግልጽ ይታወቃል:: ስለ ሕገ መንግሥት መከበርና ስለ ፌደራላዊ ሥርዓት አስፈላጊነት አበክሮ እየሰበከ፣ በተግባር ግን ምን ያህል ፀረ ሕገ መንግሥትና ፀረ ፌደራሊዝም እንደነበር እና እንደሆነ ይታወቃል:: በሁሉም መስክ በተግባር ተፈትኖ የወደቀ ድርጅት ነው:: ይህ ግፈኛ ድርጅት በሕዝቦች ትግል (ከድርጅት ውጭም በድርጅት ውስጥም በተደረገ ትግል) ተዋርዶ አፈግፍጎ መቀሌ ከትሟል::

ሕወሓት በሕዝብ ትግል ተዋርዶ ቢያፈገፍግም መስዋዕትነት የተከፈለለት የትግል አጀንዳ ግን አሁንም ፍሬ አላፈራም:: ገና ብዙ ትግል፤ ገና ከፍ ያለ መስዋዕትነት የሚያስከፍል የትግል ጊዜ ይጠብቀናል::

---

[4] *Frances Stewart (2008). Horizontal Inequalities and Conflict: Understanding Group Violence in Multiethnic Societies. Pp.3*

“

ሕወሓት በእኩልነትና ፍትሐዊነት ስም እየማለ እና እየተገዘተ፣ በተግባር ምን ያህል ፀረ እኩልነትና ፀረ ፍትሕ እንደነበር በግልጽ ይታወቃል። ስለ ሕገ መንግሥት መከበርና ስለ ፌዴራላዊ ሥርዓት አስፈላጊነት እየሰበከ፣ በተግባር ምን ያህል ፀረ ሕገ መንግሥትና ፀረ ፌደራሊዝም እንደነበር እና እንደሆነ በደንብ ይታወቃል። በሁሉም መስክ በተግባር ተፈትኖ የወደቀ ድርጅት ነው።

ሕዝባችን ከሕወሓት ውድቀት (ማፈግፈግ) ማግስት በዚህች ሀገር እኩልነት የነገሠበት ፍትሐዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዕውን ይሆናል የሚል ተስፋ የነበረው ቢሆንም፣ በሚያሳዝን ሁኔታ አሁንም በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የአሸናፊ ተሸናፊ ፖለቲካው በአዲስ መልክ እንደቀጠለ ነው። አሁንም ትግሉንና የትግሉን ፍሬ ጠቅልሎ የመዋጥ ሁኔታ በግልጽ እየታየ ነው። የአማራና የኦሮሞ ሕዝቦች ለተገኘው ለውጥ የአንበሳውን ደርሻ የሚይዝ መስዋዕትነት መክፈላቸው ሐቅ ቢሆንም፣ የአማራ ሕዝብና የክልሉ መሪ ድርጅት [አዴፓ] ወደ ዳር እየተገፉ ነው። ኦዲፒም ቁልፍ ቁልፍ የመንግሥት ኀላፊነቶች ጠቅልሎ መውሰድ ብቻ ሳይሆን ከሕወሓትም በሚብስ መልኩ ያየሁት ሁሉ አይቅረኝ የሚል እጅግ ስግብግብ የሆነ ለማንም የማይጠቅም አካሄድን እየተከተለ ነው።

በሌላ በኩል ከኦዲፒም በላይ ጽንፈኛና አክራሪ የሆኑ የኦሮሞ ኀይሎች በኦሮሞና በአማራ ሕዝቦች መካከል ያለውን መተማመን በመበጠስ፣ ከፍተኛ የሆነ የጥላቻ ቅስቀሳና አማራን የመበጥበጥ እርምጃ ውስጥ ከገቡ ሰነባብተዋል። ይህ የጥፋት ኀይሎች አካሄድ እጅግ ዘግናኝ በሆነ የሚዲያ ቅስቀሳና ፕሮፓጋንዳ ብቻ የተወሰነ አይደለም። በተግባር "በአማሮች ላይ እርምጃ ውሰዱ፤" እያሉ እስከመቀስቀስ የተደረሰበት እና ቅስቀሳው ፍሬ አፍርቶ በአማራ ሕዝብ ላይ ያነጣጠረ ሁሉንዐቀፍ ጥቃት እየተፈፀመ የሚገኝበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በዚህ ረገድ ONN እና OMN የተባሉት ሚዲያዎች የሚያደርጉትን የዘር ምንጠራ ጥሪ መከታተል የእነዚህ ኀይሎች አውዳሚ አካሄድ ምን እንደሚመስል አስረጅ ነው። ይህ በተጠናና በተናበበ ሁኔታ የሚመራ መርዘኛ ፀረ አማራ ዘመቻ በዕውቀት ላይ በተመሠረተ ትግል ካልተመከተ መዘዙ የከፋ ይሆናል።

2.2. የሕወሓት ቀጣይ የጥፋት እርምጃዎች

ሕወሓት ሀገሪቱ እንዳትረጋጋ፣ በተለይም የአማራ ሕዝብ በሰላም ውሎ እንዳያድር ያለ የሌለ አቅሙን ተጠቅሞ እየሠራ ነው። ድርጅቱ ወደፊትም በተለመደ የጥፋት ተግባሩ እንደሚቀጥልበት ብዙ ምልክቶች አሉ። አማራ ክልል የሐቀኛ ፌደራሊዝም ተምሳሌት ሆኖ ሳለ፣ ክልላዊ መንግሥቱ የሕዝቦችን መብት እንደሚጨፈልቅ ተደርጎ መጠነ-ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ሲሠራበት ቆይቷል፤ አሁንም ይህ መሠረተ-ቢስ የጥፋት ፕሮፓጋንዳ ተጠናክሮ እንደቀጠለ ነው። ሕወሓት አሁንም በክልሉ የሚገኙ ሕዝቦችን እርስ በርስ ለመከፋፈልና ጥርጣሬ ውስጥ ለመክተት በከፍተኛ ደረጃ እየቀሰቀሰና እያደራጀ እንደሚገኝ በግልጽ ይታወቃል።

አሁን ያለው ሕወሓት የፌደራል መንግሥቱን በከፍተኛ ደረጃ ተቆጣጠሮ እንደነበረው ሕወሓት ለአባላቱና ደጋፊዎቹ የሚያከፋፍለው ኪራይ (ሥልጣን፣ መሬት፣ ብድር፣ ገንዘብ ወዘተ.) የለውም። ስለሆነም ድርጅቱ በዚህ ቁመናው በክልል ደረጃ ተወስኖ ከቆየ በጊዜ ሒደት የሚያከፋፍለው ኪራይ ስለሌለ ከሕዝብ ጋር መቆራረጡ አይቀርም። ሕወሓት ከጊዜ ጋር ሽሚያ ላይ ነው።

ለዚህ ነው በክልል ደረጃ በሥልጣን ላይ ለመቆየት ሕዝቡን በማፈን፣ ትምክህተኞች መጡብህ እያለ መጠነ-ሰፊ ቅስቀሳ በማድረግ እና ሀገሪቱ ብጥብጥ ውስጥ እንድትገባ

በመሥራት ራሱን የሰላምና መረጋጋት ጠበቃ አድርጎ ማቅረብ የሚፈልገው:: የሕወሓት ህልውና ከሰላም ጋር ሳይሆን ከግጭት ጋር የተያያዘ ነው:: በሀገር ደረጃ ሰላምና መረጋጋት ካለ ሕወሓት አይኖርም፤ ዕድሜው ያጥራል፤ ራሱ የትግራይ ሕዝብ "አታሳንሰኝ፣ ከወገኖቼ ጋር አታቀራርጠኝ፤ የእስካሁኑ ይበቃሃል፤" ብሎ አንቅሮ ይተፋዋል:: የጊዜ ጉዳይ ነው::

የሕወሓት መኖርና መፋፋት ከኢትዮጵያ መዳከምና ግጭት ውስጥ መግባት ጋር በእጅጉ የተያያዘ ነው:: ስለሆነም ሕወሓት ሁልጊዜም በየአቅጣጫው እሳት በመለኮስ አማራን ብቻ ሳይሆን አጠቃላይ ኢትዮጵያን ማድማቱን ይቀጥላል:: ሕወሓት መቼም ቢሆን ለሕዝባችን የማይተኛ ደመኛ ጠላት ነው::

2.3. የፖለቲካ ሽግግር እና አክራሪ ዘውጌ ብሔርተኝነት

ዘውጌ ብሔርተኝነት (ethnic nationalism) በነገሠበት የፖለቲካ ምኅዳር ውስጥ የሚደረግ የፖለቲካ ሽግግር ሁልጊዜም ፈተና እንደሚገጥመው የታወቀ ነው:: ሁሉም፣ በተለይም ተወዳዳሪና ተፎካካሪ የሆኑት ዘውጌ ብሔርተኞች (competing ethnic nationalists) አንዱ አንዱን ጥሎ ለማለፍና የራሱን ጥቅም ብቻ ለማሳካት የሚሮጡ በመሆናቸው ፉክክሩ ለሽግግር ጊዜ ፖለቲካ ትልቅ ፈተና ነው:: እንዲህ ባለ የፖለቲካ ሁኔታ ውስጥ ሁልጊዜም ግጭት አለ፣ ስደት አለ፣ መፈናቀል አለ::

ከግጭትና የሕዝብ መፈናቀል ትርፍ የሚያጋብሱ የዘውግ ፖለቲካ ኢንተርፕረነሮች ሀገር ሰላም እንድትሆን አይፈልጉም::[5] ሁልጊዜም እንወክለዋለን የሚሉትን ሕዝብ ስሜታዊ በሆነ መልኩ እየቀሰቀሱ ወደ ግጭት አውድማ ማስገባት የዘወትር ተግባራቸው ነው:: ጭር ሲል አይወዱም:: በዚህ ምክንያት ለመጪዎቹ ዐሥርት ዓመታት በሀገራችን ዘውግ ተኮር ግጭትና የሕዝብ መፈናቀል ከፍና ዝቅ እያለ መቀጠሉ አይቀርም::[6]

ተወደደም ተጠላም ተወዳዳሪና ተፎካካሪ ዘውጌ ብሔርተኛ ኀይሎች ለመጪዎቹ 50 እና ከዚያ በላይ ዓመታት በፖለቲካ ምኅዳሩ ላይ የበላይነት ይዘው መቀጠላቸው የማይቀር እውነታ ነው:: የኢትዮጵያ ፖለቲካ በአመዛኙ በዘውጌ ብሔርተኛ ኀይሎች መካከል የሚደረግ ፉክክር ሆኖ መቀጠሉ በግልጽ የሚታይ ነው:: ይህም በራሱ ችግር አይደለም:: ችግር የሚሆነው በዘውጌ ብሔርተኞች መካከል የሚደረገው ውድድርና ፉክክር ወደ አውዳሚ ሁኔታ እንዳያመራ ቅርጽ የሚያስይዝ አስቻይ የፖለቲካ ሁኔታ (enabling political environment) አለመኖር ነው::

---

[5] እነዚህ አካላት የሕዝቡን ትግልና መስዋዕትነት ወደ መኖሪያ መጦሪያነት (commodification of pain; of death; of violence etc) የቀየሩ በላኤ-ሰቦች (monsters) ሲሆኑ፣ በተለይ በአማራው ትግል ውስጥ ትልቅ እንቅፋት ከሚፈጥሩት አካላት መካከል እነዚህ ትግሉን የእንጀራ ምንጫቸው ያደረጉ ሌቦች ግንባር ቀደም ተጠቃሽ ናቸው::

[6] Jack Snyder (2000). From Voting to Violence: Democratization and Nationalist Conflict.

ከፉክክርና መጠፋፋት ወደ መቻቻል፣ ከዚያም አልፎ ልዩነትን ይዞ ወደ መተማመንና መግባባት መምጣት የሚቻለው ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ምኅዳር ሲፈጠር ነው። ውድድሩ ጤናማ እንዲሆን የሚያስችለው ብቸኛ ማስቻያ [ሥርዓት] ዴሞክራሲ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በርካታ ዘውጌ ማኅበረሰቦች፣ ሃይማኖቶችና የተለያዩ (አንዳንዱም የማይታረቁ) የፖለቲካ አመለካከቶች ያሉባቸው ሀገሮች ብቸኛ መዳኛ መንገድ ዴሞክራሲ ነው። ኢትዮጵያም ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውጪ ምንም ዓይነት ምርጫ የላትም። ብቸኛው መዳኛዋ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ነው።

“ኢትዮጵያም ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውጪ ምንም ዓይነት ምርጫ የለትም:: ብቸኛው መዳኛዋ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ነው::

2.4. የብሉይ ዘመን ድህነት የደቀነው አደጋ

በግሉ ሴክተር አንቀሳቃሽነትና በመንግሥት ደጋፊነት/አመቻችነት የተገኘም ባይሆን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ግስጋሴ ተስፋ ፈንጥቆ እንደነበር አይዘነጋም። ሆኖም ይህ በአመዛኙ በውጭ እርዳታና ብድር ላይ ተንጠልጥሎ በመንግሥት ግንባር ቀደም አንቀሳቃሽነት የተገኘ የኢኮኖሚ ዕድገትና መነቃቃት ካለፉት ሦስትና አራት ዓመታት ወዲህ በተለያዩ ምክንያቶች መቀጠል አልቻለም፤ ይልቁንም ጉዞው የቁልቁለት ሆኗል። ኢኮኖሚው በእጅጉ ተቀዛቅዟል፤ የኑሮ ውድነቱ ሕዝብ አማሯል፤ ሥራ አጥነቱ ጣሪያ ነክቷል። ኢኮኖሚው ከፍ ያለ መዋቅራዊ ችግር እንዳለበትም መገንዘብ ያስፈልጋል።

ዛሬ በሀገራችን ሰልፍ ውጣ ሲባል እንደጎርፍ የሚወጣ፣ አቃጥል ሲባል የሚያቃጥል፣ ግደል ሲባል የሚገድል ተስፋ ያጣ ወጣት በየአካባቢው ሞልቷል። ጥራት የሌለው ትምህርትም ቢሆን በገፍ ተምሮ ያለ ሥራ የተቀመጠው ወጣት እጅግ ብዙ ነው። የሀገር ሰላምና መረጋጋት ሌላው ጠንቅ በሀገራችን የሚታየው መረን የለሽ ሥራ-አጥነት ነው።

የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ እና ድህነትና ሥራ አጥነት የግጭት ምንጭ ይሆናል። ግጭትም በፈንታው ለኢኮኖሚ ድቀት ትልቅ አስተዋጽዖ ያደርጋል። አንዱ በሌላው ላይ ተጽዕኖ አለው።[7] ለነየመን መፈራረስ እና ለብዙዎቹ የአፍሪካ ሀገሮች መታመስ ተቀዳሚው ምክንያት የኢኮኖሚው ውድቀት ነው።

አንዱና ትልቁ የሀገራችንና የሕዝባችን ፈተናም ከዚህ እውነታ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው።

2.5. ‹ኦሊጋርኪ› የደቀነው ፈተና

የጥገኝነት ፖለቲካል ኢኮኖሚ የገነገነበት አደገኛ ሁኔታ ላይ እንገኛለን። ከደርግ ቅይጥ ኢኮኖሚ ፖሊሲ እወጃ ማግስት ጀምሮ አየር ባየር በመነገድ የከበሩ፣ በኋላም በሕወሓት/ኢሕአዴግ ዘመን ከድርጅቱ ወይም ከድርጅቱ አመራሮች ጋር በተለያየ መልኩ የጥቅም ግንኙነት በመገንባት እና ኔትዎርክ በመዘርጋት በአንድ ጀንበር የከበሩ ጎይሎች (የአቶ ክቡር ገናን ቃል እንዋስና ‹የፓራሹት ነጋዴዎች›) የሀገሪቱን ፖለቲካ በፈለጉት መልኩ ለመዘወር የሚሞክሩበት እና/ወይም የሚዘውሩበት እጅግ አደገኛ ሁኔታ ተፈጥሯል። እነኝህ ጥገኛ ባለሀብቶች (‹ኦሊጋርኮች›) እነሱ የፈለጉትን ሰው ለማሾም ያልፈለጉትን ከሥልጣን ለማውረድ ወይም ወደ ሥልጣን እንዳይመጣ ለማድረግ በስፋት ይሠራሉ፤ እየሠሩም ነው።

ይህ በኢትዮጵያ ደረጃ ሥር የሰደደ የጥገኝነት አደጋ በአማራ ክልልም እያቆጠቆጠ እንደመጣ በግልጽ እየታየ ነው። የክልሉ ገዥ ፓርቲ (አዴፓ) ነባሩን የግምገማና ድርጅታዊ የትግል ባህል አዳብሮ (ወቅቱን በዋጀ መልኩ አስተካክሎ) ጠንክሮ ካልወጣ እና ክልሉን

[7] ብዙ የአፍሪካ ሀገሮችን የሚያምስ እና በስፋት የተጻፈበት ችግር ነው።

የፖለቲካ ጎይሉ ካልመራው፣ ሀገራችንም ሆነች ክልላችን የአውዳሚው ጥገኛ ባለሀብት እስረኛ መሆኑ እና ውድ ዋጋ መክፈላችን አይቀርም:: የክልሉ ገዥ ፓርቲ ከታች እስከ ላይ ካልተጠናከረ፣ ጥቂት ጥገኛ ባለሀብቶች በድርጅቱ የውስጥ ጉዳይ እየገቡ የሚፈተፍቱበት አሠራር ከሥረ-መሠረቱ ካልተነቀለ እና የአመራሩ የሕዝብ አገልጋይነት ቁርጠኝነት በፍጥነት ካልተሻሻለ ከፊት ለፊታችን የሚጠብቀን ተጨማሪ ሽንፈት ነው::

ጥገኛው ባለሀብት የፖለቲካ ጎይሉን እንደፈለገ በማሾር እሱን የሚጠቅም የጨረታ፣ የኢንቨስትመንት ወዘተ... *መመሪያ* ያስወጣል:: እንደ ብሔራዊ ከበርቴ በላቡ በደሙ ሀብት ስለማያፈራ እና በነጻ ገበያ ኢኮኖሚ ውስጥ የመወዳደር አቅም ስለሌለው ለሌሎች ኢንቨስተሮች ምቹ ሁኔታ እንዲኖር ጨርሶ አይፈልግም:: ይልቁንም ሌሎች ኢንቨስተሮች እንዳይመጡ መንግሥታዊ ቢሮክራሲውን ጭምር በመጠቀም ባለ በሌለ አቅሙ መሰናክል ይፈጥራል::

ጥሮ ግሮ ሀብት ያፈራ ብሔራዊ ከበርቴ ሌሎች ኢንቨስተሮች መምጣታቸው ተጨማሪ የገበያ ዕድል እንደሚፈጥር እና የቢዝነስ መነቃቃትን እንደሚያመጣ ስለሚገነዘብ ሁልጊዜም ከእሱ ውጪ ላሉ ኢንቨስተሮች ያለው እይታ በጎ ነው:: የፓራሹት ነጋዴው በአንጻሩ ተጠራጣሪ፣ ሴረኛና ተናዳፊ በመሆኑ የኢንቨስትመንት ከባቢውን በማወክ ይታወቃል:: ብሔራዊ ከበርቴው ሩቅ ዓላሚ ሲሆን የፓራሹት ነጋዴው በአንጻሩ የእይታ አድማሱ እጅግ ጠባብ ነው፤ ርዕይ የለውም፤ የሀገርና የወገን ጉዳይ ጉዳዩ አይደለም፤ ለሕዝብ *ሠራሁ* ካለም ተጨማሪ ጥቅማ ጥቅም (የመሬት፣ የታክስ እፎይታ ወዘተ...) ለማግኘት የሚያደርገው የቅጥፈት እርምጃና ርካሽ የሕዝብ ግንኙነት *ሥራ* ነው:: ይህ ጎይል የትኛውንም መንገድ ተጠቅሞ በአጭር ጊዜ ሀብት ማከበት ነው ተቀዳሚ ዓላማው::

ትልቁ የአፍሪካ ሀገራት ፈተና ከጥገኛ ከበርቴዎች አካባቢ የሚመጣው ነው:: እነኝህ ጎይሎች በመንግሥት ላይ ሌላ ትይዩ/ተደራቢ መንግሥት ለመፍጠር ከፍተኛ ጥረት ያደርጋሉ፤ ካልሆነም የመንግሥትን ቢሮክራሲና አቅም ተጠቅመው በቢሮክራሲው አማካይነት የራሳቸውን ጉዳይ ለማስፈፀም አበክረው ይሠራሉ:: ጥገኛ ጎይሎች ትልቅ የሰላም፣ መረጋጋትና የልማት ጠንቅ ናቸው:: አንዳንድ ጊዜ የጦር አበጋዝነትን ሚና ወስደው የራሳቸውን *ሠራዊትና* መቺ ጎይል እስከማደራጀት ይሄዳሉ:: ኢመደበኛ በሆነ ንግድ [ለምሳሌ የመሣሪያ ንግድ ወዘተ...] ውስጥ ስለሚዘፈቁ እና የጦርነት/የግጭት ኢኮኖሚ በእጅጉ ስለሚጠቅማቸው ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን አይፈልጉም:: በተቀናቃኝ የፖለቲካ ድርጅቶችም ይሁን በተገዳዳሪ/ተፎካካሪ የአንድ ድርጅት ፖለቲከኞች መካከል ልዩነትን በመፍጠር ድርጅቶችንና መንግሥታዊ *ሥልጣንን* በእጅ አዙር ለመቆጣጠር ይሠራሉ:: ባለሥልጣን በገንዘብ ይገዛሉ፤ ያስፈራራሉ፤ ካስፈለገም ይገድላሉ:: ሌላም ሌላም::[8]

---

[8] *"... [A] Shadow state relates to the informal commercial networks that operate parallel to state bureaucracies and undermine formal governance. Even if state agents are involved, according to Reno, these networks have their own channels of exploitation and commercialization outside of the state" (Reno 2000).*

ከፖለቲካ አመራሩ ጋር በልዩ ልዩ መንገድ ኔትዎርክ በመፍጠር በአጭር ጊዜ ሀብት የሚያጋብሱት እነዚህ አካላት፣ ኢኮኖሚስቶች እንደሚሉት ከዘርፎ-ሄያጅ ሽፍታነት (robbing bandit) ወደ “መደበኛ የቢዝነስ ሰውነት” (stationary bandit) ሊቀየሩ የሚችሉት ጠንካራ የፖለቲካ አመራር እና ጥርስ ያለው መንግሥታዊ አቅም (መዋቅር) ሲኖር ብቻ ነው:: መንግሥት ጠንካራ ሕግና ሥርዓት የማስከበር፣ የማስፈፀም እና የመፈፀም አቅም ከሌለው የፓራሹት ነጋዴዎችና የጦር አበጋዞች መፈንጫ መሆኑ የማይቀር ሐቅ ነው::

በጊዜ መስመር መያዝ ያለበት የሀገራችንም ሆነ የአማራ ሕዝብ [ተጨማሪ] ፈተና ይህ ነው::

3. ምን ይሻላል?

3.1. የፋክክር ሳይሆን የትብብር ዘመን መሆኑን መገንዘብ

በኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ጎይሎች መካከል ሊኖር የሚገባው ፉክክር ሳይሆን ትብብር ነው:: በተለይም በአማራ ድርጅቶች እንዲሁም በአማራ ድርጅቶችና በልሂቃኑ መካከል ሊኖር የሚገባው ትብብር ብቻ ነው:: ያለንበት እጅግ አደገኛ የፖለቲካ ሁኔታ ፉክክርን የሚመጥን አይደለም:: የሚያዋጣው መተባበር፣ መተራረም፣ መወያየትና መላ መምታት ብቻ ነው::

በፖለቲካ ልሂቃኑ መካከል ለበርካታ ዓመታት ሰፍኖ የቆየው አለመተማመን እንዲሰበር ክክልሉ ገዥ ፓርቲ (አዴፓ) ብዙ ይጠበቃል:: ድርጅቱ በአንድ በኩል የተሻለ የፖለቲካ ግንዛቤ እና የሕዝብ ተቆርቋሪነት ያላቸውን ምሁራን ወደ ድርጅቱ ለመሳብ ከፍተኛ ሥራ መሥራት ይገባዋል:: አዴፓ ምሁራንን የሚፈራ፣ ምሁራንም አዴፓን በአሽከርነት የሚከሱና የሚጠራጠሩ መሆን የለባቸውም:: ይህ አደገኛ አካሄድ በፍጥነት መታረም ይገባዋል:: ምሁሩም የማኅበራዊ ሚዲያ ጠማሪውም አዴፓን መቀጥቀጥን እንደ ሥራ ከመቁጠር ወጥቶ መፍትሔ ማፍለቅና የመፍትሔው አካል መሆን ይገባዋል:: አዴፓን መቀጥቀጥ ሥራ አይደለም፤ አይጠቅመንም፤ አልጠቀመንም::

“አዴፓ ከአፈጣጠሩ የመነጨ ችግር አለበት፤ ከቶውንም ሊሻሻል አይችልም፤ በድን ነው፤ ጋንግሪን ነው፤ መቆረጥ አለበት፤” ወዘተ... እየተባለ ያልተጻፈ ጽሑፍ የለም፤ በዚህ ድርጅት ላይ ያልወረደበት ውርጅብኝ የለም:: አልጠቀመንም:: ወደፊትም እንዲህ ዓይነቱ የፖለቲካ ሽታ የሌለው፣ የአማራን ሕዝብ በምንም ዓይነት መንገድ የማያግዝ እና ከለቅሶና እሮሮ በስተቀር መፍትሔ የማያቀርብ አካሄድ አይጠቅመንም::

የተሻለውና ሕዝብ ሊጠቅም የሚችለው አካሄድ አዴፓ አልሠራም ከተባለ እንዲሠራ ማገዝ ወይም እሱን ሊተካ የሚችል ጠንካራ አማራጭ ሐሳብና ድርጅት ማቅረብ ነው:: ለመሆኑ ከአዴፓ ውጪ ያለው አማራ ከማለቃቀስ ወጥቶ ድርጅቱን ለማገዝ ምን ጥረት አድርጓል? ምን ዓይነት ሕዝብ ሊጠቅም የሚችል ሐሳብ አመነጨ? ምን ዓይነት ጠንካራ ሲቪክና የፖለቲካ ድርጅቶችን ፈጠረ? ምን ዓይነት ተቋማትን ገነባ? ከለቅሶና እርግማን ያለፈ ሕዝብን ሊጠቅም የሚችል ምን ምን ተግባራትን አከናወነ?

እውነቱን እንነጋገር ከተባለ የአማራ ልሂቅ ከግብዝነት (hipocracy) ወጥቶ ሕዝባችንን የሚያሻግሩ ሐሳቦችን በማፍለቅና ጠንካራ የሲቪክና የፖለቲካ ድርጅቶችን በመፍጠር ረገድ ያደረገው ይህ ነው ተብሎ ሊጠቀስ የሚችል ሥራ የለም። ዳር ቆሞ አዬፓ አይረባም፤ አብን አይጠቅምም ማለት ምሁርነት አይደለም። የምሁርነት መለኪያው ሕዝብን ሊያሻግር የሚችል ሐሳብ ማፍለቅ ነው፤ ምሁርነት ወገናዊነትን ከሕዝብ ጋር አድርጎ ለሕዝብ መታገል ነው።

ሁሉንም ችግር በአዬፓ ወይም በአብን ላይ መደፍደፉ ውጤት አላመጣም፤ ሊያመጣም አይችልም። ግብዝነት ይብቃን፤ እንቀየር!

ያለንበት እጅግ አደገኛ የፖለቲካ ሁኔታ
ፋክክርን የሚመጥን አይደለም ። ።

እንደ አብን ያሉ የፖለቲካ ድርጅቶችም አባሎቻቸውን በሚገባ ማሰልጠንና በዕውቀት ማስታጠቅ ይኖርባቸዋል:: አብን የሕዝብ ትግልና መገፋት የወለደው፣ በርካቶች ተስፋ የሚያደርጉበት ድርጅት ነው:: በአጭር ጊዜ ውስጥ ሕዝቡን በማነቃቃት ረገድም ቀላል የማይባል አስተዋጽዖ አድርጓል:: ይሁን እንጅ አብን በዚህች አጭር ጊዜ ውስጥ ሕዝባችንን ውድ ዋጋ ያስከፈሉና ወደፊትም የሚያስከፍሉ ትልልቅ ስህተቶችን የፈፀመ ድርጅት መሆኑም ሊሰመርበት ይገባል:: አብን እንደ ሕወሓት ያሉ ፀረ አማራ ኀይሎች ሕዝባችንን ጭራቅ አድርገው በመሳል ረገድ የፈፀመውብንን ገጽታችንን የማጠልሸት ሥራ በሌላ መንገድ ያስቀጠለ ድርጅት ነው:: አንዳንድ የአብን አመራሮች በጀብደኝነት የተናገሯቸው ንግግሮችና የጻፏቸው ጽሑፎች ከፍተኛ የሆነ የሕዝብ ግንኙነት ቀውስ ውስጥ ከትተውናል፤ በሌሎች ሕዝቦች ዘንድ በከፍተኛ ጥርጣሬ እንድንታይ አድርገውናል::

ስለሆነም እያንዳንዱ የአብን አመራርም ይሁን የድርጅት አባል የሚጽፈው ጽሑፍ ወይም የሚናገረው ንግግር በሕዝባችን ላይ ምን ያህል ጣጣ ሊያመጣ እንደሚችል ማወቅና መብሰል ይገባዋል:: አውቀን በጀብደኝነትም ይሁን ድጋፍ ያስገኝልኛል በሚል ስሌት ወይም ባለማወቅ የምንጽፈው ንግግር እና የምናደርገው ንግግር ሕዝባችንን ውድ ዋጋ ሊያስከፍል እንደሚችልና እያስከፈለንም እንደሆነ በደንብ መገንዘብ ይገባል::[9]

በታሪክ አጋጣሚ ሕዝባችን በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ተሰራጭቶ ይገኛል:: የሕዝባችን ስርጭት በአግባቡና በዕውቀት ከተጠቀምንበት ትልቅ ሀብት ሲሆን፣ ባግባቡ ካልተጠቀምንበት ግን ትልቅ ዕዳ ነው::[10] ስለሆነም የአማራ ድርጅቶች እና የማኅበራዊ ሚዲያ ጦማሪያን ይህንን የሕዝባችንን ልዩ ሁኔታ በሚገባ መገንዘብ እና ተናበው መሥራት ይገባቸዋል::

የአማራ ፖለቲካ ከኦሮሞ፣ ከትግራይ ወይም ከሌሎች ሕዝቦች ፖለቲካ በእጅጉ እንደሚለይና መለየትም እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል:: የአማራ ፖለቲካ ከአማራ ሕዝብ ታሪክ፣ ዕሴትና ነባራዊ ሁኔታ አንጻር መታየትና መቃኘት ይገባዋል:: እያንዳንዱ ሕዝብ የየራሱ ልዩ (essential) ሁኔታ አለው:: አማራም እንዲሁ:: ስለሆነም ፖለቲካችንም ይህንን የሕዝባችንን ልዩ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ያስገባ እንዲሆን ያስፈልጋል::

የኦሮሞ ድርጅቶች እንዲህ ስላደረጉ እኛ እንዲህ እናድርግ፣ የትግራይ ድርጅቶች እንዲያ ስላደረጉ እንዲያ እናድርግ ወዘተ... የምንለውን የአጀንዳ መለቃቀም አካሄድ በፍጥነት ማረም ይገባናል::[11] ስለ አማራ እንጻፍ፤ እንከራከር፤ እንወያይ:: ለአማራ እንሥራ::

---

[9] [አብን] በዋና ተቀናቃኙ [ኢዴፓ] ውስጥ በተከሰተ ችግር ከአዴፓ በላይ መታመሱ ስለ አብን ድርጅታዊ አቅም የሚናገረው ብዙ ነገር አለ፡፡ የሰኔ 15ቱ ክስተት በሕዝባችን ላይ ሊያመጣ የሚችለውን አደጋ በተመለከተ በዕውቀትና በአርቆ አሳቢነት ላይ የተመሠረተ ግምገማ በማድረግ ሕዝብ የማረጋጋት ሥራ መሥራት ሲገባ በአብን አመራሮች መካከል የተስተዋለው ሽኩቻና መጠላለፍ እጅግ የሚዘገንን ነው፡፡ አሁንም ቢሆን፣ ይህ አደገኛ አዝማሚያ በሚገባ ተገምግሞ አስፈላጊው የእርማት እርምጃ ካልተወሰደ ውሎ አድሮ ሕዝባችን ተጨማሪ ዋጋ መክፈሉ አይቀሬ ነው፡፡

[10] ሕዝባችን በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች ተሰራጭቶ መገኘቱ ሁልጊዜም እንደ አዳ መታየት የለበትም፡፡ ይልቁንም ከሌሎች ሕዝቦች ጋር ለምናደርገው ጤናማ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነትና መስተጋብር ከፍተኛ አስተዋጽዖ ሊያደርግ እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

[11] ለምሳሌ ሕዝባችን ኢትዮጵያን በመገንባት ረገድ የነበረው ግንባር ቀደም ሚና፣ በሀገር ግንባታ ፕሮጀክቱ ምክንያት በሁሉም የሀገሪቱ ክፍል ተሰራጭቶ መገኘቱ፣ የቋንቋችንና ባህላችን አቅም ወዘተ... ከሌሎች ሕዝቦች ይለየናል፡፡

ሕዝባችን ከሌሎች ጎይሎች ጋር ተደራድሮ መብቱንና ጥቅሙን ሊያስከብር የሚችለው በራሳችን የውስጥ ጉዳይ ላይ ስንሠራ እና አቅማችንን ስንገነባ ብቻ ነው። ውስጣዊ ጎብረታችንና አንድነታችንን በሚገነቡ ጉዳዮች ላይ ሳንሠራ ወደ ውጭ ብናንጋጥጥ ትርፉ ውድቀት ነው። ከትናንት እስከ ዛሬ የአማራ ሕዝብ ግንባር ቀደም ጠላት ራሱ አማራ ነው፤ ትልቁ ድክመታችንና የውድቀታችን ምንጭም ይኸው ከውስጣዊ አንድነታችን አለመጠናከር የመጣ ነው።

3.2. በአማራነትና ኢትዮጵያዊነት መካከል ያለውን መስተጋብር መገንዘብና ማስገንዘብ

አማራ ማን ነው? አማራነትስ ምንድን ነው? በአማራነትና ኢትዮጵያዊነት መካከል ያለው መስተጋብር ምንድን ነው? ወዘተ... በሚሉት መሠረታዊ ጥያቄዎች ላይ ተመሳሳይም ባይሆን ተቀራራቢ ግንዛቤ መጨበጥ በጣም አስፈላጊ ነው።[12]

አማራነት ከሁሉም በላይ "አማራ ነኝ" ብሎ ማመን ነው። አማራነት አማርኛ ቋንቋን መናገር እና/ወይም ለአማርኛ ቋንቋ መቆርቆር፤ በአማራ ታሪክ፣ ባህልና እሴት መኩራት፣ መጠበቅ፣ መንከባከብና ማሳደግ፤ በአማራ ትውፊት፡- በተረትና ምሳሌው፣ በቅኔው፣ በሽምግልናው፣ በአንቱታው፣ በእስክስታው፣ በቀረርቶው፣ በሽለላው፣ ወዘተ... መኩራት እና ትውፊቱን መጠበቅና መንከባከብ ነው። አማራነት ከሌሎች አማሮች ጋር የምጋራው ታሪክና ባህል አለኝ ብቻ ሳይሆን መጻኢ ዕድሌም ከእነሱ ጋር የተቆራኘ ነው ብሎ ማመን ነው። አማራነት ልክ እንደ ጀግኖች አርበኞች እምቢ ባይነትን እና በሽንፈት ወቅት አልሸነፍም ብሎ በጽናት መቆምንም ይጨምራል። እምቢታና ተጋድሎ (defiance and resistance) ዓይነተኛ መለዮዎቹ የሆኑ ማንነት ነው አማራነት። አማራነት ሌሎችም በርካታ መገለጫዎች አሉት።

አማራነትና ኢትዮጵያዊነት የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው። የአማራ ሕዝብ ኢትዮጵያን በመገንባትና በመጠበቅ ያደረገው አስተዋጽዖ እጅግ ትልቅ ነው። አማራነት ዘውጋዊ ማንነታችን ሲሆን፣ ኢትዮጵያዊነት ደግሞ አጥንታችን የከሰከስንለት፣ ደማችንን ያፈሰስንለት እና ወደፊትም የምንሰዋለት ዜግነታዊ ማንነታችን ነው። ሁለቱ ማንነቶች እርስ በርሳቸው የሚጠፋፉ ሳይሆኑ በእጅጉ ተመጋጋቢዎች ናቸው። ለአንዱ መኖር ሌላው አስፈላጊ ነው። የአማራ ሕዝብ መደራጀትና መጠናከር ለኢትዮጵያ መጠናከር ያለው አስተዋጽዖ ከፍተኛ ነው። የኢትዮጵያ መጠናከርና መልማትም የአማራ ሕዝብ ልማት ነው። በዚህ መሠረታዊ እውነታ ላይ ሁሉም የአማራ ልጆች የጋራ ግንዛቤ እንዲኖራቸው መሥራት ይገባል።

---

[12] *የየትኛውንም ሕዝብ ማንነት በሚመለከት አንድ ሁሉን የሚያስማማና ያለቀለት ብያኔ መስጠት አይቻልም፤ ሁልጊዜም ልዩነቶችና ከርከሮች ይኖራሉ። በእንግሊዝነት፣ ስኮቲሽነት፣ ራሻነት፣ ስፓኒሽነት ወዘተ... ላይ ተመሳሳይ ግንዛቤም ሆነ ሁሉንም የሚያስማማ ብያኔ የለም። ቁም ነገሩ ሁሉንም የሚያስማማ ወይም ጥያቄ የማይነሳበትና "የማያንጠባጥብ" (watertight) ብያኔ መኖሩ አይደለም። ዋናው ቁም ነገር በሕዝቡ ወሳኝ (overarching) መለዮዎች ላይ ተቀራራቢ የሆነ የጋራ ግንዛቤ መኖሩ ነው።*

3.3. የጦማሪያኑን ሚና መገንዘብና ሚናቸውን ለይቶ በአግባቡ መጠቀም

ተወደደም ተጠላም በዚህ ዘመን ማኅበራዊ ሚዲያ በሀገራችን ብቻ ሳይሆን በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ትልቅ አቅም ያለው ኀይል ነው:: ይህን ትልቅ አቅም ሚናውን በአግባቡ ጥቅም ላይ ካዋሉት ትልቅ የሰላም፣ የመረጋጋትና የልማት ኀይል ይሆናል:: በአግባቡ ጥቅም ላይ ካልዋለ የሚያደርሰውን ኅብረተሰባዊ ውድመት ደግሞ ከእኛ ሕዝብ በላይ የሚያውቀው የለም፤ ብዙ ደምተንበታል::

የአማራ ማኅበራዊ ሚዲያ ጦማሪያን የሕወሓትን ግፈኛ ቡድን በመዋጋት፣ በብአዴን ውስጥ ሲታይ የነበረውንና አሁንም በአዴፓ ውስጥ የሚታየውን ድክመት በማጋለጥ፣ ኢፍትሐዊነትን በመታገል ወዘተ... ረገድ ያደረጉትና እያደረጉት ያለው አስተዋጽዖ የሚናቅ አይደለም:: በተለይ የተወሰኑ ቁርጠኛና የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው ጸሐፊዎች ለአማራ ሕዝብ ኅብረትና ለብሔርተኝነት ግንባታው ያደረጉት አስተዋጽዖ ደግሞ በጣም ከፍ ያለ ነው:: ሆኖም በማያከራክር ሁኔታ የሚበዛው የማኅበራዊ ሚዲያ ጸሐፊ ከመገንባት ይልቅ በማፍረስ ላይ አተኩሮ የሚንቀሳቀስ ነው:: በዚህ ረገድ ማኅበራዊ ሚዲያው ለሰኔ 15 ክስተት ያደረገውን አስተዋጽዖ፣ ከዚያም በኋላ የፈጠረውን ውድመት ማየት ‹አክቲቪስቱ› ምን ያህል አውዳሚ ኀኒ እንደሚያመዝን በግልጽ የሚያሳይ አብነት ነው::

የማኅበራዊ ሚዲያ ጦማሪያን በአማራ ድርጅቶችና በክልሉ መንግሥት ባለሥልጣናት መካከል ጥርጣሬና ክፍፍል እንዲፈጠርና ክፍፍሉ አድጎ ወደ እርስ በርስ መጠፋፋት እንዲሄድ ከፍተኛ ሚና መጫወታቸውን መቀበል ያስፈልጋል:: አንዱን በማኮሰስ ሌላውን በማጀገን የፈጠሩት ስንጥቅ እና ስንጥቁ ያስከተለው ውድመት ከፍተኛ ነው:: ከሰኔ 15 ማግስት ጀምሮ የታየው እጅግ ዘግናኝና ሕዝባችንን ለተጨማሪ ሽንፈት የሚያመቻች አካሄድም ውድ ዋጋ እያስከፈለን ይገኛል:: አሁንም ብዙሃኑ የማኅበራዊ ሚዲያ ጦማሪ በስሜት የሚጋልብ ነው:: አሁንም [በአመዛኙ] ማኅበራዊ ሚዲያውን የበከለው በሬ ወለደ ነው:: የሚበዛው የአማራ ማኅበራዊ ሚዲያ ጦማሪ ኀላቀርና የዕውቀት ችግር ያለበት፣ ከመገንባት ይልቅ በማጠልሸትና ማፍረስ ላይ የሚያተኩር፣ ሕዝቡ ይቅደም የሚል ሳይሆን በግለሰብ ተክሰ-ሰብዕና ግንባታ ላይ የተጠመደ፣ አጀንዳ አፍላቂና አስቀማጭ ሳይሆን የሰው አጀንዳ ሲለቃቅም የሚውል ነው ማለት ይቻላል::

ስለሆነም ሁሉንም ባይቻል ብዙሃኑን የማኅበራዊ ሚዲያ ጦማሪያን አቅጣጫና ቅርጽ ሊያስይዝ የሚችል፣ ይልቁንም አዳዲስና ዕውቀት ጠገብ የሆኑ ጦማሪያንን እያበረታታ ወደፊት ሊያመጣ የሚችል [በመደበኛም ይሁን ኢመደበኛ በሆነ መልኩ] የተደራጀ ጠንካራ ስብስብ ያስፈልገናል:: ይህ ስብስብ በድርጅት ደረጃ ሳይታጠር አማራ እንደ አማራ እንዴት ሊሰባሰብ እንደሚገባ፣ በምን መልኩ መብቱንና ጥቅሞቹን ሊያስከብር እንደሚችል፣ የገጠሙት ፈተናዎች ምን ምን እንደሆኑ፣ ፀረ አማራ ኀይሎችን እንዴት መመከት እንደሚቻል ወዘተ... በዕውቀት ላይ ተመሥርቶ እየተነተነ አቅጣጫ የሚያስይዝ መሆን ይገባዋል::

አበው እንደሚሉት “ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው” ነውና የማኅበራዊ ሚዲያ ጦማሪያንና “አክቲቪስቶች” የሚጽፉትን ነገር በሚገባ ማጣራት ይኖርባቸዋል:: በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ወይም ሌላ ተልዕኮ ይዘው የአማራን ሕዝብ የሚጎዳ ነገር የሚፅፉ አካላትን የሚያጋልጡና እውነቱን ለሕዝብ እያሳወቁ አቅጣጫ የሚያስይዙ ተቆርቋሪ የአማራ ልጆችን ማፍራት ያስፈልጋል::

“የማኅበራዊ ሚዲያ ጦማሪያን በአማራ ድርጅቶችና በክልሉ መንግሥት ባለሥልጣናት መካከል ጥርጣሬና ክፍፍል እንዲፈጠርና ክፍፍሉ አድጎ ወደ እርስ በርስ መጠፋፋት እንዲሄድ ከፍተኛ ሚና መጫዎቱን መቀበል ያስፈልጋል::

3.4. የገጠመንን የሕዝብ ግንኙነት ቀውስ በፍጥነት ማረም

የአማራ ሕዝብ ኢትዮጵያ ውስጥ ፍትሐዊና እኩልነት የሰፈነበት ሥርዓት እንዲገነባ ከማንም በላይ ታግሏል:: እነ ብላታ ታከለ ወልደ ሐዋሪያት ከዘውዳዊ ይልቅ ሪፐብሊካዊ ሥርዓት ያስፈልገናል ብለው ከማንም በፊት ተሟግተዋል፤ ታግለው መስዋዕትነትም ተቀብለዋል:: የነዋይ ልጆች (መንግሥቱና ግርማሜ)፣ ኮ/ል ወርቅነህ ገበየሁ፣ ጀኔራል ጽጌ ዲቡ እና ሌሎች የአማራ ልጆች ፍትሐዊነት የሰፈነበት ሥርዓት ለመመሥረት በዐፄ ኀይለ ሥላሴ አገዛዝ ላይ መፈንቅለ መንግሥት ሞክረው መስዋዕትነት ከፍለው ለተከታዮቹ የመብትና የእኩልነት ታጋዮች አርአያ ሆነው አልፈዋል::

አንጋፋ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ እና የድርጅት መሪዎች፤ በተለይም እንደ ዶ/ር ወርቁ ፈረደ፣ ዶ/ር ከበደ መንገሻ፣ ዶ/ር እልሁ ፈለቀ፣ ዶ/ር ነገደ ጎበዜ፣ አቶ ዮሐንስ አድማሱ፣ አቶ አንዳርጋቸው አሰግድ፣ ዶ/ር የራስወርቅ አድማሴ፣ ዶ/ር አክሎግ ቢራራ፣ ዶ/ር አማረ ተግባሩ እና ሌሎች በሺሕዎች የሚቆጠሩት የመኢሶን አመራሮችና አባላት፤ እንዲሁም እንደ ነጋ አየለ፣ ጸጋዬ ገብረ መድኅን (ደብተራው)፣ ክፍሉ ታደሰ፣ ዋስልኝ መኮንን፣ ዶ/ር ዮናስ አድማሱ፣ ዶ/ር መላኩ ተገኝ፣ ግርማቸው ለማ፣ ጌታቸው ማሩ፣ ሕይወት ተፈራ፣ ወዘተ... ያሉት በመቶ ሺሕዎች የሚቆጠሩ የኢሕአፓ አመራሮችና አባላት፤ እንዲሁም የሌሎቹ ድርጅቶች መሪና አባል የአማራ ልጆች ምን ያህል ለፍትሕና እኩልነት እንደታገሉና መስዋዕትነት እንደከፈሉ ታሪክ የመዘገበው፣ ሀገር ያወቀው ሐቅ ነው::

አሁን ላለንበት መከራ ከዳረጉን ጉዳዮች አንዱ የአማራ ልጆች የገባር ሥርዓቱን ተፋልመው ለፍትሕና እኩልነት ያደረጉትን ተጋድሎ በሚገባ አለመረዳታችንና አለማስረዳታችን ነው::

ፀረ አማራ ኀይሎች የፈጠራ ድርሰት እያዘጋጁ ሕዝባችንን በጨፍላቂነትና ጨቋኝነት አበክረው እየከሰሰ ውርጅብኝ ሲያወርዱበት በእኛ በኩል ሐቁን መሠረት አድርጎ መመከት አልተቻለም:: በማያጠያይቅ ሁኔታ የሕዝብ ግንኙነትና የፕሮፓጋንዳ ብልጫ ተወስዶብናል:: የአማራ ልጆች ከማንም በላይ ለእኩልነት፣ ፍትሕና ዴሞክራሲ መስዋዕት ሆነው ሳለ መስዋዕትነታቸው መና እንዲቀር አድርገነዋል፤ ስለ ሃይማኖቶችና ብሔሮች እኩልነት ከማንም በላይ የታገሉት የአማራ ልጆች ሆነው ሳለ ትግላቸውንና መስዋዕትነታቸውን አልተጠቀምንበትም:: ይህ ሁኔታ በፍጥነት መታረም ይገባዋል::

የአማራ ሕዝብ በሀገራችን እኩልነት፣ ፍትሕና ዴሞክራሲ የሰፈነበት ሥርዓት እንዲገነባ የከፈለው መጠነ-ሰፊ መስዋዕትነት በአግባቡ ለሕዝብ መቅረብ አለበት:: በዚህ ረገድ የፖለቲካ ድርጅቶች ካድሬዎችና አባላት፣ የተቀናቃኝ ድርጅቶች ካድሬዎችና አባላት፣ ምሁራን፣ የማኅበራዊ ሚዲያ ጦማሪያንና ‹ሜንስትሪም› ሚዲያው (አማራ መገናኛ ብዙሃን እና አሥራት) እየተናበቡ ሚናቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል::

አንዱና ዋናው የፀረ አማራ ኀይሎችን የጥፋት ትርክት ማርከሻ መሣሪያ ሕዝባችን የከፈለውን ዋጋ በሚገባ በሐቅና በዕውቀት ላይ ተመሥርቶ ማስረዳት ነው::

የእኛ መደራጀትና መጠናከር ለሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዕድል እንጅ የስጋት ምንጭ አለመሆኑን አበክረን ማስገንዘብ ይኖርብናል:: ተደራጅተን ሌሎችን የመጨቆን ዓላማ እንደሌለን ማስረዳት ይገባናል:: ብቻችን እንብላ፣ ብቻችን እንምራ እንደማንል፤ ታሪካችንም እሱን እንደማያሳይ፤ የእኛ ትግል እንደ ሕዝብ ተደራጅተን አማራዊ ህልውናችንን መስከበርና ሁሉንም ሕዝቦቿን በእኩልነት የምታስተናግድ ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንድትኖር የሚደረግ ትግል መሆኑን ደጋግመን መግለጽ ይገባናል:: በዚህ ረገድ፣ ሁሉም የአማራ ልጅ [የሕዝቡ] አምባሳደር ሆኖ መሥራት ይገባዋል::

“

አሁን ላለንበት መከራ ከዳረጉን ጉዳዮች አንዱ የአማራ ልጆች የገባር ሥርዓቱን ተፋልመው ለፍትሕና እኩልነት ያደረጉትን ተጋድሎ በሚገባ አለመረዳታችንና አለማስረዳታችን ነው::

3.5. በቆምንለትው መሠረታዊ መርሆዎች/ዒለማዎች ላይ የጋራ ግንዛቤ መፍጠር

የትግላችን ምሰሶዎች እኩልነት፣ ፍትሕ፣ ዴሞክራሲና ልማት ናቸው። የአማራ ሕዝብ መሠረታዊ ጥያቄዎች እኩልነት የሰፈነባት፣ ፍትሐዊነት የነገሠባት፣ ከድህነት የተላቀቀች ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ናቸው።

አንዱ ከፍ ሌላው ዝቅ የማይልባት ኢትዮጵያ ዕውን እንድትሆን ከማንም በላይ መታገል ያለብን እኛ ነን። ፍትሐዊ የፖለቲካ ውክልናና ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት እንዲሰፍን ከማንም በላይ መታገል ያለብን እኛ ነን። በክልላችንና ሕዝባችን ልማት ላይ መረባረብ ያለብን እኛው ነን። በዚህች ሀገር ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲገነባ ከማንም በላይ መታገል ያለብን እኛ ነን። ዴሞክራሲ የተደቀነብንን የህልውና አደጋ ከመከትን በኋላ የምንገነባው የቅንጦት አጀንዳ ሳይሆን የህልውና አደጋውን መመከቻው መንገድ ነው።

ሐቀኛ ዴሞክራት ሳንሆን ሌሎች የዴሞክራሲ ኀይሎችን ከጎናችን ማሰለፍ ከቶውንም አንችልም። ሐቀኛ የፍትሕና እኩልነት ኀይል ሳንሆን ከሌሎች ዴሞክራት ኀይሎች ጋር በመተማመን ልንሠራ የምንችልበት ዕድል የለም። ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር የሚኖረን ግንኙነት በእኩልነት፣ በመከባበርና በሰጥቶ መቀበል መርህ ላይ የተመሠረተ እንዲሆን ያስፈልጋል።

የአማራ ሕዝብ ጥያቄዎች ሁሉ በእጃችህ በአራቱ መርሆዎች አማካይነት የሚፈቱ ናቸው። እኩልነትን እንስበክ፣ ስለ ፍትሕ እንታገል፣ ልማትን እናፋጥን፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲገነባ እንታገል።

“የአማራ ሕዝብ ከፍትሕ፣ እኩልነትና ዴሞክራሲ
የሚያጣው አንዳች ነገር የለም።”

3.6. የትግል ቅደም ተከተል ማስቀመጥ

ብዙዎቹ ጥያቄዎቻችን ተደጋግሞ እንደሚባለው በሥራ ላይ ባለው ሕገ መንግሥት ምክንያት የተፈጠሩ አይደሉም:: ይልቁንም ብዙዎቹ ጥያቄዎቻችን ሕገ መንግሥቱ ሳይሸራረፍ በሥራ ላይ ቢውል የሚፈቱ ናቸው::[13] እንዴት?

[በአማራ ልጆች] ተደጋግመው የሚቀርቡ ሕገ መንግሥቱን የሚመለከቱ የተወሰኑ ነጥቦችን ጠቅሰን ጉዳዩን ለመስረዳት እንሞክር:: አንደኛው ነጥብ ሕገ መንግሥቱ "እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች..." ብሎ መጀመሩን የሚመለከተው ነው:: ስለ አማራ [ብሔር] እያወራን "ሕገ መንግሥቱ ስለ ዜግነት መብት አይገደውም፤ ስለዚህም መሻሻል አለበት፤" ማለት ግራ የሚያጋባ ነገር ነው::

ኹለተኛው ነጥብ ደግሞ በሕዝቦች መካከል የተዛባ ግንኙነት ነበር ተብሎ በሕገ መንግሥቱ የተጠቀሰውን ጉዳይ የሚመለከተው ነው:: በኢትዮጵያ ሕዝቦችና መንግሥት መካከል የነበረውና ያለው ግንኙነት (State-society relation) ጤናማ ሆኖ እንደማያውቅ በግልጽ ይታወቃል፤ ግንኙነቱ የተዛባ መሆኑም እውነት ነው::

ይህ ብቻ አይደለም:: በሀገራችን ሕዝቦች መካከልም የሰመረ ግንኙነት ነበረ ወይም አለ ማለት አይቻልም:: ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ብሔራዊ ሃይማኖት እንደነበርና ቤተ ክርስቲያኒቱም ከፍተኛ ሚና እንደነበራት ይታወቃል:: ይህ በራሱ በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ እና በሌሎች ሃይማኖቶች መካከል የደረጃ ልዩነት እንደነበር አስረጅ ነው:: አሕመድ ግራኝ የኢትዮጵያን መንግሥታዊ ሥልጣን ለመቆጣጠር ባደረገው ጦርነት ያደረሰው ውድመትም ሌላ የተዛባ ግንኙነት ምንጭ ነው:: የኦሮሞ ሕዝብ መስፋፋት በደቡብና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ላይ ያደረሰው መጠነ-ሰፊ ውድመትም በሕዝቦች መካከል የነበረው ግንኙነት የተዛባ መሆኑን አስረጅ ነው:: የኢትዮጵያ ሀገረ-መንግሥት እንደገና በዳግማዊ ዐፄ ምኒልክ መሪነት ሲገነባ የደረሰው ሰብአዊ ቀውስ፣ በተለይም በኂላ የመጣው ጭሰኝነትም ሌላው የተዛባ ግንኙነት ምንጭ ነው::[14] በሀገራችን የጾታ እኩልነት ነበር ማለትም ፈፅሞ አይቻልም::[15] ስለነበሩትና እስካሁንም ድረስ ስለቀጠሉት የተዛቡ ግንኙነቶች ሌሎች በርካታ አብነቶችንም መጥቀስ ይቻላል::

---

[13] እዚህ ላይ መግለጽ የምንወደው መሠረታዊ ቁም ነገር፣ በሥራ ላይ ያለው ሕገ መንግሥት እንከን የለሽ ነው፣ ስለሆነም መሻሻል የለበትም እያልን አለመሆኑን ነው:: የእኛ ሙግት:- "የችግሮቻችን ሁሉ ምንጭ ይህ ሕገ መንግሥት ነው መባሉ ትክክል አይደለም፤ ይልቁንም ሕገ መንግሥቱ በትክክል በሥራ ላይ ቢውል የሚበዙት የአማራ ሕዝብ ጥያቄዎች መልስ ያገኛሉ፣ እስካሁንም የሕገ መንግሥት ይቀየር ጥያቄን የትግላችን አልፋና ኦሜጋ ማድረጋችን ትክክል አልነበረም፣ ከፍተኛ የሆነ የቅደም ተከተል ችግር ገጥሞናል፣ እንደ ሕወሓት ዓይነት ፀረ ዴሞክራሲያዊ ኀይሎች በየደቂቃው ሕገ መንግሥቱን እየጣሱ የዚህ ሰነድ ዋስ ጠበቃ/ተራማጅ ሆነው ሲቀርቡ እኛ በአንጻሩ የምናራምደው አቋም ፀረ ሕገ መንግሥትና ፀረ ፌደራሊዝም ተደርገን እንድንቆጠር አድርጎናል፣ ይህም በሌሎች ሕዝቦች ብቻ ሳይሆን በዓለም ዐቀፍ ማኅበረሰቡም ዘንድ በጥርጣሬ እንድንታይ አድርጎናል፣" የሚል ነው::

[14] የሀገረ-መንግሥት ግንባታ ፕሮጀክቱ ሌላ የተዛባ ግንኙነትን እንዳስቀረም መታወቅ አለበት:: ለምሳሌ ያህል በኦሮሞ ነሳዎች መካከል፣ ከዚያም አልፎ በኦሮሞ ነሳዎችና በሌሎች ሕዝቦች መካከል ሲደረግ የነበረው የማያባራ ግጭት እንዲቆምና ሰላም እንዲፈጋገጥ ያደረገው የሀገረ-መንግሥት ግንባታ ፕሮጀክቱ ነው::

[15] በሀገራችን "መሬት ላራሹ" ብለው ጭሰኝነትን በማንበር ቀደምትነት የታገሉትና መስዋዕትነት የከፈሉት የአማራ ልጆች መሆናቸውን ማስረዳት አልቻልንም:: በደፈናው ያን ትውልድ ስንቀጠቅጥና ያደረጉትን የሚክበርና የሚያስከብር የፍትሕና እኩልነት ተጋድሎም ጥላሸት ስንቀባ ከርመናል:: መታረም ያለበት ትርክት ነው:: ካጠፉት በላይ በጎ ሚና የነበራቸው፣ በብዙ ረገድ አርአያቸውንም ልንከተል የሚገባን የሕዝብ ልጆች ናቸው::

ይህ ታሪካዊ ሐቅ ባለበት ሁኔታ ሕገ መንግሥቱ “የተዛባ ግንኙነትን ለማረም …” ማለቱ አማራን ብቻ ዒላማ አድርጎ እንደቀረበ መቆጠር የለበትም:: “የተዛባ ግንኙነት ነበር” ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ማስረዳት ያለብን እኛ ነን::

ከፍ ብሎ እንደተገለፀው በሀገራችን በሕዝቦችና መንግሥታት መካከል፣ ከዚያም አልፎ በሕዝቦች መካከል የነበረው ግንኙነት የሰመረ ነበር ማለት አይቻልም:: ይህ ሁኔታ አሁንም አልተሻሻለም:: አሁንም በመንግሥትና በሕዝቦች መካከል ያለው ግንኙነት በጎ‘ና ተገዥ መካከል ያለ ግንኙነት ነው:: አሁንም የኢትዮጵያ ሕዝቦች በዴሞክራሲያዊ መንገድ የተመረጠ መንግሥት እያስተዳደራቸው አይደለም:: አሁንም በፖለቲካ ልሂቃኑና በሰፊው ሕዝብ መካከል ያለው ግንኙነት ጤናማ አይደለም:: አሁንም እንደ ትናንቱ ከአንድ ዘውግ የወጡ የፖለቲካ ልሂቃን ሀገሪቱን እነሱ በሚፈልጉት መልኩ ሊያሾሯት እየሠሩ ነው::

ሕገ መንግሥቱ ሲረቀቅም ሆነ ሲፀድቅ አልተሳተፍንበትም፣ ስለሆነም ባልተሳተፍንበት ሕገ መንግሥት የመገዛት ግዴታ የለብንም የሚል ተደጋግሞ የሚነሳ የመከራከሪያ ነጥብ አለ:: እውነት ነው፤ የአማራ ሕዝብ በመረጣቸው ወኪሎቹ አማካይነት ይህን ሕገ መንግሥት በማርቀቅም ሆነ በማዕደቅ ሒደት አልተሳተፈም:: ሆኖም በወቅቱ በመረጣቸው ወኪሎቹ ሕገ መንግሥቱን በማርቀቅም ሆነ በማዕደቁ ሒደት የተሳተፈ አንድም ሕዝብ እንደሌለ ደግሞ የሚታወቅ ሐቅ ነው:: ጉዳዩ ሁሉንም የኢትዮጵያ ሕዝቦች የሚመለከት ጉዳይ ነው:: ጥያቄው “ሕዝባችን ከሚገኝበት ወቅታዊ የፖለቲካ አረንቋ አንጻር ትኩረታችን መሆን ያለበት በሕገ መንግሥቱ ይዘት ላይ ነው ወይስ በረቀቀበትና በፀደቀበት ሒደት ላይ?” የሚለው ነው:: ያለ ጥርጥር አትራፊ የምንሆነው በይዘቱ ላይ አተኩረን ብንሠራ ነው:: የሰነዱ ይዘት በብዙ መልኩ ሕዝባችንን የሚጠቅም ነውና::[16]

ስለሆነም የተወሰኑ አንቀጾችን እየጠቃቀስን ሕገ መንግሥቱ እንዲቀየር ወይም እንዲሻሻል ከምንሠራው ሥራ በላይ ሕገ መንግሥቱ በትክክል በተግባር ላይ እንዲውል ልንታገል ይገባናል::

ሕገ መንግሥቱ የሕወሓት ማኒፌስቶ ነው ይባላል:: ኢሳያስ አፈወርቂ፣ መለስ ዜናዊና ሌንጮ ለታ በረሃ ቁጭ ብለው ያዘጋጁት ሰነድ ነው እየተባለም ብዙ ተነግሯል:: ሕወሓትም በገቢር ፀረ ሕገ መንግሥት ሆኖ ሳለ የዚህ ሕገ መንግሥት ፊታውራሪና ጠበቃ ሆኖ እንደሚቀርብ ይታወቃል:: እነ አቶ ሌንጮም ይህንን ትርክት በደስታ ተቀብለውታል:: “ይህ ሕገ መንግሥት እንከን የለሽ ነው፤ ሕገ መንግሥቱ ከተነካ ሀገር ይታመሳል፤ ይፈርሳል፤” እያሉ በተደጋጋሚ ሲናገሩ ይደመጣሉ:: በተግባር የሚያራምዱት አቋም ግን ፀረ ሕገ መንግሥት ነው:: ይህም ስለ ሕገ መንግሥት መከበር የሚጮኹት ከልባቸው እንዳልሆነ፣ ሕገ መንግሥቱንም በቁርጠኝነት እንዳማያከብሩትና እንደማይደግፉት የሚያሳይ እውነታ ነው::

---

16 እንደ እውነቱ ከሆነ፣ ብዙ ሰዎች [የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ጭምር] ሕገ መንግሥቱን የሚቃወሙት ስለ ሰነዱ በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው ሳይሆን በስሚ ስሚ ያነጇትን መረጃ መሠረት በማድረግ ነው:: በቂ ግንዛቤ ኖሯቸው ከዜግነት ፖለቲካ አንጻር የሚቃወሙት አካላት የሉም ማለት አይደለም፤ በደንብ አሉ:: እኛ ግን [የአማራ] ብሔርተኞች ነን:: ስለሆነም የዜግነት ፖለቲካ አራማጆችን ሐሳብ ይዘን መንጎድ የለብንም::

ሕገ መንግሥቱ ስለ ሰብአዊ መብቶች መከበር በስፋት ያትታል። ይህ ደግሞ ከማንም በላይ የአማራ ልጆች የታገሉለትና መስዋዕትነት የከፈሉለት አጀንዳ ነው። ሕገ መንግሥቱ ስለ ብሔረሰቦች እኩልነትና መብት መከበር ይደነግጋል። ይህም የአማራ ልጆች የታገሉለትና የሞቱለት አጀንዳ ነው። በመቶ ሺሕዎች የሚቆጠሩ አማራ ልጆች ለሕዝቦችና ሃይማኖቶች እኩልነት ታግለዋል። የአማራ ልጆች ለእኩልነት፣ ለፍትሕ፣ ለዴሞክራሲና ለሕዝቦች ሁለንተናዊ ልማት ታሪክ የማይዘነጋው መስዋዕትነት ከፍለዋል። ይህ ሕገ መንግሥት የአማራ ልጆች መስዋዕትነት ከከፈሉላቸው አጀንዳዎች ውጪ የያዘው ብዙም ነገር የለም።

ስለሆነም መታገል ያለብን "ሕገ መንግሥቱ ሳይሸራረፍ በሥራ ላይ ይዋል ብለን እንጅ ሕገ መንግሥቱ አይወክለንም፤ ስለሆነም ይቀየር፤" ብለን መሆን የለበትም። ሕገ መንግሥት ይከበር ስንል ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሁሉም ሀገሪቱ አካባቢዎች ተንቀሳቅሶ የመኖር፣ የመሥራትና ንብረት የማፍራት መብቱ ይከበር እያልን ነው፤ ሕዝቦች በቋንቋቸው ይዳኙ፣ ይማሩ እያልን ነው፤ የሃይማኖት እኩልነት ይከበር እያልን ነው፤ መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው እያል ነው፤ የቤጎች ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይከበሩ እያል ነው ወዘተ...

ግልጽ መሆን ያለበት፣ ከዚህ ሕገ መንግሥት በተቃራኒ የቆሙት ሕወሓት፣ ኦነግና መሰሎቻቸው ናቸው። አንድ የማያሻማ አብነት ለማቅረብ የኦሮሚያ ክልል ሕገ መንግሥት ኦሮሚያ ክልልን ለኦሮሞዎች ብቻ በመስጠት ከሀገሪቱ ሕገ መንግሥት በተቃራኒ የቆመ ነው። የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ሕገ መንግሥትም ተመሳሳይ ነው። ከአማራ ክልል ሕገ መንግሥት ውጪ ያሉት አብዛኞቹ የክልል ሕገ መንግሥቶች ከሀገሪቱ ሕገ መንግሥት ጋር ተቃርነው የቆሙ ናቸው፤ ስለሆነም ኢሕገ-መንግሥታዊ ናቸው። መታገል ያለብን ይህንን ነው።

ከሀገሪቱ ርዕሰ-ሕግ ጋር የሚቃረን የክልል ሕገ መንግሥት እያወጡ የእኛ ከሚሉት ሕዝብ ውጪ ያለውን ኢትዮጵያዊ መብት የሚነፍጉ አካላት ናቸው ፀረ ሕገ መንግሥት አቋም እያራመዱ ያሉት። ጨፍላቂዎች "አዲስ አበባ የኦሮሞ ናት፤" ሲሉ ፀረ ሕገ መንግሥት መሆናቸውን በግላጭ እያስመሰከሩ መሆኑን ማወቅ ይስፈልጋል። ሕወሓት ወልቃይትንና ራያን የወሰደው ሕገ መንግሥቱ ስለሚፈቅድለት አይደለም፤ ፀረ ሕገ መንግሥት በመሆኑ ነው። የወልቃይትና የራያ አማራ ማንነት አስመላሽ ኮሚቴዎች ስለ ሕገ መንግሥት መከበር አበክረው የሚታገሉት ይህንን ሐቅ ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ነው። ይህን መሠረታዊ ሐቅ በደንብ መገንዘብ ያስፈልጋል።

በሥራ ላይ ያለው ዘውግ ተኮር ፌደራላዊ ሥርዓትም ቢሆን አማሮችን ይጠቅመናል እንጅ የሚጎዳን ምንም ነገር የለም። በመሠረቱ ዘውግ ተኮር ፌደራሊዝም እንደ ስዊትዘርላንድ፣ ቤልጀም፣ ስፔን፣ ካናዳ፣ ሕንድ ወዘተ... ያሉ ሀገሮች ሁሉ የሚከተሉት ልዩነትን ማስተናገጃ መንግሥታዊ አወቃቀር ነው። ዘውግ ተኮር ፌደራላዊ ሥርዓት የግጭትና የብተና ምክንያት የሚሆነው ከፀረ ዴሞክራሲ ጋር የተያያዘ እንደሆነ ነው። የአማራ ክልል በታሪክ አጋጣሚ [ለክፉ ታስቦም ይሁን ለበጎ] በክልሉ ውስጥ የሚገኙ ሕዝቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት አረጋግጦ ሐቀኛ የሆነ ፌደራላዊ አሠራርን

እየተገበረ የሚገኝ ክልል ነው:: [17]

በእነዚህና በሌሎች በርካታ ምክንያቶች ሕገ መንግሥቱና ፌደራላዊ ሥርዓቱ እንዲቀየር የምንቀሰቅሰው ቅስቀሳም ሆነ የምናወጣው ጉልበት (‹ኢነርጅ›) ጨርሶ ወቅታዊነት የለውም:: ሐቁን እንነጋገር ከተባለ በዚህ ወቅት አማራ መታገል ያለበት በሥራ ላይ ፌደራላዊ ሥርዓት እንዲቀጥልና ሕገ መንግሥቱ በትክክል በሥራ ላይ ያለው እንዲውል ነው:: “ሕገ መንግሥት ይከበር!” የሚለውን መፈክር መደጋገም ያለብን እኛ ነን:: የሕገ መንግሥት ጠበቆችና ሐቀኛ ፌዴራሊስት ኀይሎች ሆነን መቅረብ ያለብን እኛ ነን:: ክልላችን ከሌሎች ክልሎች በላይ ልዩነትን በመስተናገድ ምሳሌ ሆኖ ሳለ ተመልሰን በሥራ ላይ ያለውን ፌደራላዊ ሥርዓት መቃወማችን መታረም ያለበት ትልቅ ተቃርኖ ነው::

ቅድሚያ መሠራት ያለባቸውን ተግባራት ቅድሚያ ሰጥተን እንከውን:: የትግል ቅደም ተከተል ይኑረን!

---

[17] *[እንደ ጽንፈኛ የኦሮሞ ብሔርተኞች] በክልል ደረጃ የፌደራሉን ሕገ መንግሥት የሚቃረን ሕገ መንግሥት አፅድቆ የሌሎች ብሔረሰቦችንና ዜጎችን መብት እየጨፈለቁ ስለ ሕገ መንግሥት መከበር መስበክ እና ፌደራሊስት ኀይል ነኝ እያሉ መናገር ተራ ቅጥፈትና ማጭበርበር ነው:: በማያሻማ ሁኔታ የእነኝህ ኀይሎች መገለጫ ፀረ ሕገ መንግሥትነትና ፀረ ፌደራሊስትነት (ጨፍላቂነት) ነው:: ጽንፈኛ የኦሮሞ ብሔርተኞች መንግሥታዊ ሥልጣኑን ያለተቀናቃኝ ተቆጣጥረው ለመቆየት እንዲያስችላቸው የሚያደራጁት “የኩሽ ኅብረት” የተሰኘ ስብስብ በግልጽ የሚያሳየን እነኝህ አካላት ፌደራሊስት ሳይሆኑ አሃዳዊ መሆናቸውን ነው:: እኛ ከሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች ጋር የሚኖረንና ሊኖረን የሚገባው ኅብረት ዴሞክራቲክ ኅብረት ብቻ ነው::*

“

ብዙዎቹ ጥያቄዎቻችን ተደጋግሞ እንደሚባለው በሥራ ላይ ባለው ሕገ መንግሥት የተፈጠሩ አይደሉም። ይልቁንም ብዙዎቹ ጥያቄዎቻችን ሕገ መንግሥቱ ሳይሸራረፍ በሥራ ላይ ቢውል የሚፈቱ ናቸው።

3.7. ሰኔ 15ን በጥበብ መሻገር

ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም. በክልላችን የተፈፀመው የከፍተኛ አመራሮች ግድያ ትግላችንን በእጅጉ ወደኋላ የወሰደ፣ በአማራ ሕዝብ ጎብረት ላይም ከፍተኛ አደጋ የደቀነ ክስተት ነው:: አደጋው በሁሉም መስክ የከሰርንበት ብቻ ሳይሆን በጥበብና በአርቆ አስተዋይነት ካልፈታነው ወደፊትም እየተከተለ ሊያቆስለን የሚችል አደገኛ ክስተት ነው::[18] ስለሆነም ያ አደጋ ለምን እንደተፈጠረ፣ እንዴት እንደተፈጠረ እና በሕዝብ መካከል የተፈጠረውን ቁስል ለመጠገን ምን ማድረግ እንደሚሻል በሐቅ ላይ የተመሠረተ ውይይት ማድረግ ይገባል:: ሕዝባችን እውነቱን ማውቅ ይገባዋል፤ የማወቅ መብትም አለው::

በዚያ ድርጊት እና በድርጊቱ ተዋናዮች ላይ መግባባት ሊኖር ይገባል:: ሐቁ ከታወቀ በኋላ ጉዳዩን ሌላ የውጭ ኀይል ሳይገባበት በአማራ ሕዝብ ባህል መሠረት በእርቅና በሽምግልና መጨረስ ይቻላል:: ሐቁ ተድበስብሶና ተሸፋፍኖ ከቀረ ግን ይህ ጉዳይ አዴፓንም፣ አብንንም ሌሎችንም ድርጅቶቻችን የሚያምስ፤ ሁልጊዜም የልዩነትና አለመተማመን ምንጭ ሆኖ የሚቀጥል ጉዳይ ነው::

በዚህ ረገድ የክልሉ ገዥ ፓርቲ [አዴፓ] ከማንም በላይ የበሰለና ዘመን ተሻጋሪ የሆነ አመራር እንዲሰጥ ይጠበቃል:: ሐቁ እንዲወጣ እና ጉዳዩ በሕዝቡ ዕሴት መሠረት በእርቅና ሽምግልና እንዲዘጋ ማድረግ ያስፈልጋል:: ሰኔ 15ን በአግባቡ ካልተሻገርነው ግን ጣጣችን ይቀጥላል!

አለመደማመጥ እና በዕውቀትና በስክነት አለመመራት ሲያስጠቃን ኖሯል፤ ወደፊትም ይገድለናል:: እኔ ብቻ ነኝ ትክክል የሌሎች ሐሳብ አይረባም ማለት ለሽንፈት ዳርጎናል፤ ወደፊትም ቀውስ ውስጥ ይከትተናል:: ከሐሳቡ ይልቅ ሐሳቡን ያመነጨ ሰዎችን መዋጋት ውድ ዋጋ አስከፍሎናል፤ ወደፊትም ዋጋ እንከፍልበታለን::

ከገጠመን የጋራ ሽንፈት በሚገባ ተምረን ወደፊት መሄድ ይገባናል:: የሐሳብና የአመለካከት ልዩነቶች በኀይል ሳይሆን በክርክርና በውይይት እንዲፈቱ ያስፈልጋል:: ዴሞክራሲያዊ አስተሳሰብና አሠራር ሊሰርፀን ይገባል::

በራሳችን የውስጥ ችግር ምክንያት የገጠመንን ትልቅ ሽንፈት በሰከነ ሁኔታ በዕውቀት ላይ ተመሥርተን ከፈተሸነው ለአማራ ብሔርተኝነት ግዙፍ አቅም ይሆናል፤ ያጣናቸው ወንድሞቻችን ደምም በከንቱ ፈስሶ አይቀርም:: የሐሳብና የአመለካከት ልዩነትን በሰከነና በሰለጠነ መንገድ አለማስተናገድ ሊያስከትልብን የሚችለውን አደጋ ከሰኔ 15 በላይ ሊስረዳን የሚችል ክስተት የለም::

---

[18] *[ክስተቱ] እንደ መልካም ኢጋጣሚ ይቆጠር ከተባለ ያ ክስተት በግልጽ ያሳየን ነገር፣ የአማራ ብሔርተኝነት ምን ያህል እንዳልጠና እና ምን ያህል በቀላሉ ችግርን የመቋቋም ፈተና ውስጥ ሊገባ እንደሚችል ነው፡፡ በአንድ ድርጅት ውስጥ የተፈጠረ ችግር አጠቃላይ ብሔርተኝነቱን እና ብሔርተኛውን ኀይል በከፍተኛ ደረጃ ሲያምሰው ተስተውሏል፡፡ [በሁሉም ጎራ] ብዙዎች ተፈትነው የወደቁበት የታሪካችን ጥቁር ነጥብ ነው፡፡*

“

የሐሳብና የአመለካከት ልዩነትን በሰከነና በሰለጠነ መንገድ አለማስተናገድ ሊያስከትልብን የሚችለውን አደጋ ከሰኔ 15 በላይ ሊስረዳን የሚችል ክስተት የለም::

3.7. የደሞክራሲ ጮራ የምትፈነጥቅበት ክልል መፍጠር፤ የኬራላ አብነት

አማራ ክልል የኢትዮጵያ የፍትሕ፣ እኩልነትና ዴሞክራሲ ጮራ የሚፈነጥቅበት ክልል መሆን ይችላል፤ ይገባዋልም:: ክልሉ የኢንቨስትመንት መዲና መሆን ይችላል፤ ይገባዋልም:: ለኢንቨስትመንት መበረታታት ደግሞ ሰላምና መረጋጋት በጣም አስፈላጊ ነው:: ስለሆነም ክልሉ የሰላምና መረጋጋት ደሴት እንዲሆን ያስፈልጋል:: ከራሳችን ግላዊ ጥቅም ይልቅ ሕዝባችን የገባበት አረንቋ የሚያንገበግበን ከሆንና በቁጭት ከተነሳን ይህንንም ማድረግ የሚከብድ ነገር አይደለም::[19]

በዚህ ረገድ ትልቅ አብነት ልትሆነን የምትችለው ኬራላ የተሰኘችው የሕንድ ግዛት/ክልል ናት:: ኬራላ የልማታዊና ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ፈለግን በመከተል የለማችና አርአያነት ያላት የሕንድ ግዛት ስትሆን፣ በአንድ ፌደራላዊ ሀገር ውስጥ አንድ ክልል በልዩ ሁኔታ በሁለንተናዊ መልኩ ሊለማና ለሌሎችም ምሳሌ ሊሆን እንደሚችል ያስመሰከረች ግዛት ናት:: የሕንድ የዴሞክራሲና የልማት ጮራ የፈነጠቀባት ግዛት!

ኬራላ መልካም አስተዳደርን የሚያሰፍን ጠንካራ የሕዝብ አስተዳደር ሥርዓት፣ እንዲሁም ጠንካራና ዘመናዊ ሲቪል ሰርቪስ ገንብታለች:: በዴሞክራሲ ረገድም፣ በጣም በርካታና ጠንካራ ሲቪል ማኅበራት፣ መገናኛ ብዙሃን፣ የጥቅም (interest groups) እና የሙያ ማኅበራት በነጻነት የሚንቀሳቀሱባት አሳታፊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት (participatory democracy) የገነባች ግዛት ናት::

የአማራ ክልል ፍትሕ፣ እኩልነትና ዴሞክራሲ የነገሡበት ክልል እንዲሆን በማድረግ፣ የክልሉን የሕዝብ አስተዳደር ሥርዓት (public adminstration) በዕውቀት ላይ ተመሥርቶ በማዘመን እና ጠንካራና ዘመናዊ ሲቪል ሰርቪስ በመገንባት ለሌሎች የኢትዮጵያ ክልሎች አርአያ መሆን ይችላል፤ ይገባዋልም::

በክልላችን ከፍተኛ የሆነ የውጭና የሀገር ውስጥ የኢንቨስትመንት መሳብ ካልተቻለ ትልቅ አደጋ ነው:: ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ደግሞ ከምንም ነገር በላይ ጠንካራና ዘመናዊ ቢሮክራሲ ያስፈልጋል:: ኢንቨስትመንት ሰላምና መረጋጋትንም በእጅጉ ይፈልጋል:: በክልላችን ዘላቂ የሆነ ሰላምና መረጋጋት እንዲኖር ካስፈለገ ደግሞ ዴሞክራሲ የግድ ነው:: በክልሉ ሕዝቦች መካከል ፍትሐዊና እኩልነት የሰፈነበት ሥርዓት መገንባትም በጣም አስፈላጊ ነው::[20]

---

[19] በክልላችን ከየትኛውም አካባበቢና ሀገር የሚመጣን ሰው በፍቅር ተቀብለን የማስተናገድ ነባር ዕሴታችንን አዳብረንና አዘምነን ማስቀጠል ይገባናል። አማራ ክልል ማንም ሰው "ማህ? ከየት ነህ?" ሳይባል፣ በጸጸት የሚኖርበትና ንብረት የሚያፈራበት ክልል መሆን ይገባዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚታዩ አደገኛ አዝማሚያዎች ታላቁን የአማራ ሕዝብ ጨርሶ የማይመጥኑ ስለሆኑ ሁላችንም እምርረን ልንዋጋቸው ይገባል። ክልሉ የጦር አበጋዞች መፈንጫ ሳይሆን ሰላም የሰፈነበት የኢንቨስትመንት መዲና የሆነ ክልል እንዲሆን ማድረግ የክልሉ መንግሥት ብቻ ሳይሆን የሁላችንም ኀላፊነት ነው።

[20] የአማራ ክልል መንግሥት እና ሕዝብ ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ማርኬቲንግ እና/ወይም የሕዝብ ግንኙነት ችግር አለባቸው:: ክልሉ የሕዝቦችን የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን በማክበር ረገድ ከየትኛውም የሀገሪቱ ክልል በላይ ከፍ ያለ ሪከርድ ቢኖረውም ያለውን ነገር ለሌሎች በማስረዳት ረገድ ትልቅ ችግር ይታይበታል:: በዚህ ምክንያት ያለ ስሙ ስም ሲሰጠው ይስተዋላል:: ለአማራ ሕዝብ ከአገው ሕዝብ የሚቀርበው የለም፣ ለአገው ሕዝብም ከአማራ ሕዝብ የቀረበ ወንድም የለውም:: አንድም ሁለትም የሆኑ፣ ያለፈው ታሪካቸውና ባህላቸው ብቻ ሳይሆን መጻኢ ዕድላቸውም የተሳሰረ ሕዝቦች ናቸው:: ወደረኞቻችን በእነዚህ አንድም ሁለትም በሆኑ ሕዝቦች መካከል እየገቡ ነው ሊያናክሱን የሚፈልጉት:: እነሱ ግን በተግባር እንደታየው የሕዝቦችን መብት በመድፈቅ የሚታወቁ ፀረ ዴሞክራሲና ፀረ ፍትሕ ናቸው::

ሀብት አላነሰንም፤ ሞልቶናል:: ክልላችን በተፈጥሮ ሀብት የበለፀገ በመሆኑ በዕውቀትና በቁጭት ከተመራ እንኳን ለክልሉ ሕዝብ ለሌላውም ሊተርፍ የሚችል ነው:: የኢትዮጵያ ትልቁ ወንዝ የሚገኘው አማራ ክልል ውስጥ ነው:: ትልቁ ሐይቅ የሚገኘው አማራ ክልል ውስጥ ነው:: ትልቁ ተራራ የሚገኘውም በዚሽው ክልል ነው:: ከዚህም በላይ፤ አማራ ክልል በጣም በርካታ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ ሀብቶች ያሉት ግዙፍ ክልል ነው:: በደንብ ካለማነው የሕዝባችን ቁጥርም በራሱ ትልቅ ሀብት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል:: እኛ ያጣነው ያለንን እምቅ የተፈጥሮና ሰው ሠራሽ ሀብት አቀናጅቶ መሥራትና ማሠራት የሚችል የመሪነት አቅምና ቁርጠኝነት ነው:: ይህ ችግር ደግሞ የአንድ ድርጅት ወይም ቡድን ችግር ብቻ አይደለም፤ ማኅበረሰባዊ ችግር ነው:: እንደ ሕዝብ ወድቀናል፤ ያለንበት አሳፋሪ ሁኔታ ፈጽሞ አይመጥነንም:: ቁጭት ሊያድርብን ይገባል!

ሕዝባችን የሚገኝበት እጅግ አሳዛኝ ኋላቀርነት፣ ያለንበት ከታሪካችን ጋር ጨርሶ የማይሄድ የአመራርና የዕውቀት ድህነት እና ባለንበት ሁኔታ ከቀጠልን የሚጠብቀን ተጨማሪ መከራ ሊያንገበግበን ይገባል:: አማሮች በሁሉም መስክ በራሳችን ላይ አብዮት ማካሄድ ያስፈልገናል:: የፖለቲካ ባህላችን በመሠረታዊነት መቀየር አለበት:: የሥራ ባህላችንና ለሥራ ያለን ክብር ከሥረ-መሠረቱ መቀየር ይገባዋል:: ለጊዜ የምንሰጠው ግምትም አብዮት ያስፈልገዋል::

አሉባልታውን፣ እጣት መጠቀሙንና መጠላለፉን ትተን ራሳችንና ሕዝባችንን በሚቀይሩ ተግባራት ላይ እንጠመድ:: መቆጨት፣ መምከር፣ መደራጀት፣ መፍትሔ ማፍለቅ እና ወደ ተግባራዊ እርምጃ መግባት ይገባናል:: ጊዜ የለንም፤ በጊዜ የለንም መንፈስ እንሥራ!!!

3.8. የአማራ ብሔርተኝነትን ማጽናት

የአማራ ብሔርተኝነት በሕዝቡ ላይ የተደቀነውን የህልውና አደጋ ለመመከት፤ የአማራን ታሪክ፣ ባህልና ትውፊት ጠብቆ ለሚቀጥለው ትውልድ ለማስተላለፍ፤ ሕዝባችን ተደራጅቶ በቁጭት መንፈስ ከተደቀነበት የብሉይ ዘመን ድህነት እንዲወጣ ለማስቻል የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው:: የአማራ ብሔርተኝነት የትኛውንም ሕዝብ በጠላትነት ፈርጆ አይንቀሳቀስም::

በእርግጥም ሻዕብያ፣ ሕወሓትና ኦነግ የአማራን ሕዝብ በጠላት ፈርጀው እንደተነሱት እኛም አንድን ሕዝብ በጠላትነት መፈርጅ ይኖርብናል ማለት አይደለም:: በመሠረቱ ብሔርተኝነት የግድ ጠላት ያስፈልገዋል የሚለው አስተያየት መሠረት የለውም:: የራስን ህልውና ለመጠበቅ ጠላት ፈርጆ መንቀሳቀስ የግድ አይደለም፤ የራስን ቋንቋ፣ ታሪክ፣ ባህል፣ ትውፊት ወዘተ... ለመጠበቅ፣ ለማሳደግና አበልጽጎ ለቀጣዩ ትውልድ ለማስቀጠል መደራጀት ጠላት ፈርጆ መንቀሳቀስን አይጠይቅም:: ተደራጅቶ እና ተደጋግፎ ከድህነት ለመውጣትና ለመልማት ጠላት አያስፈልግም::

ስለሆነም የአማራ ብሔርተኝነት ይህ ወይም ያ የሚለው በጠላትነት የፈረጀው ሕዝብ የለም፤ ሊኖረውም አይገባም:: በዚህ ምክንያት የአማራ ብሔርተኝነት በሀገር ደረጃ ለሚደረገው የፍትሕ፣ እኩልነትና የዴሞክራሲ ትግል ትልቅ አጋር ነው:: ለዚህ ነው

አማራ ብሔርተኝነት ይበልጥ መጠናከር፣ ይበልጥ እየጎመራና እየበሰለ መሄድ አለበት የምንለው::

እዚህ ላይ ግልጽ መሆን ያለበት ቁም ነገር፣ ከትናንት እስከ ዛሬ የአማራን ሕዝብ በጠላትነት ፈርጀው የተንቀሳቀሱ እና አሁንም የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ኀይሎች የሉም ማለት አይደለም:: ነበሩ፤ አሁንም አሉ::

ፋሽስት ኢጣሊያ ሕዝባችንን በሰነድ ደረጃ በጠላትነት ፈርጆ መጠነ-ሰፊ ቅስቀሳ አድርጓል፤ ሌሎች የኢትዮጵያ ሕዝቦች በአማራ ሕዝብ ላይ በጠላትነት እንዲነሱም በብዙ ሠርቷል፤ ቀላል ያልሆነ ስኬትም አግኝቶበታል::[21] የፋሽስት አስተምህሮ ወራሽ የሆኑ እንደ ሕወሓትና ኦነግ ያሉ የፖለቲካ ቡድኖችም ከትናንት እስከዛሬ ሕዝባችንን እንዳደሙት ይገኛሉ:: አሁንም የአማራ ሕዝብ ሰላም አግኝቶ እንዳይለማ ከየአቅጣጫው በእሳት እየለበለቡት ነው:: ይህ የፀረ አማራ ቡድኖች የጥፋት ተግባር ወደፊትም ተጠናክሮ ይቀጥላል::

ከእኛ ከአማራ ልጆች የሚጠበቀው፣ የቀደሙት አባቶቻችን እንዳደረጉት ሕዝባችንና ሀገራችንን እየጠበቅንና እያለማን፣ የትኛውንም ሕዝብ እንደ ሕዝብ በጠላትነት ሳንፈርጅ ሊያዳክሙን የሚመጡትን የጥፋት ቡድኖች በበቂ ሁኔታ መመከት ነው:: ራስን መከላከልና መመከት ተፈጥሯዊ መብት በመሆኑ ማንም ሕዝባችንን ሊያተራምስ የሚመጣን ኀይል በቁርጠኝነትና በጀግንነት መታገል ይገባናል:: በዚህች ሀገር እኩልነትና ፍትሐዊነት የነገሠበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲመጣ እንታገል ስንል ሌሎች ሲቀጠቅጡን አይተን እናዳላየን እንለፍ ማለታችን አይደለም:: እኩልነትና ፍትሐዊነት እንዲሰፍን እንታገላለን፤ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲገነባ እንሠራለን:: ሰላምና ደህንነታችን የሚያደፈርስ ኀይል ሲገጥመን ደግሞ በጽናት ራሳችንን እንከላከላለን::

ራስን ከጠላት ለመከላከል ግን ስንቅና ትጥቅን በበቂ ሁኔታ ማሟላት ያስፈልጋል:: ጠንካራ የኢኮኖሚ አቅም መገንባት በጣም አስፈላጊ ነገር ነው:: የሕዝብ አንድነትና ኀብረት ደግሞ ከምንም ነገር በላይ ወሳኝ ነው:: ኀብረት የሌለውና እርስ በርሱ የሚበላላ ሕዝብ የተኩላዎች መጫዎቻ ከመሆን አይድንም:: አማራዊ ኀብረትና አንድነት ከምንም በላይ ግዙፍ ሀብት ነው፤ ትልቅ አቅም ነው::[22]

እንደ ብረት የጠነከረ አማራዊ አንድነት ይኑረን!!!

---

[21] በፋሽስት ኢጣሊያ ፀረ አማራ ቅስቀሳ ተማርከው በሕዝባችን ላይ መጠነ-ሰፊ ውርጅብኝ ስላወረዱ ኀይሎች ለመረዳት የአቶ ታደሰ ሜጫን "ጥቁር አንበሳ"፣ የደራሲ ሐዲስ ዓለማየሁን "ትዝታ" እና የአልበርቶ ስባቺን መጽሐፎች ማየት ይጠቅማል፡፡

[22] አማራዊ አንድነት ምን ያህል አስፈላጊና ወቅታዊ እንደሆነ በበቂ ሁኔታ ለመረዳት ደራሲና ጉጣሚ አበረ አዳሙ በአማራ ምሁራን መሳከርት ጉባኤ ላይ ያቀረበውን "ለምን?" የተሰኘ አስደማሚ ግጥም ደጋግሞ ማዳመጥ ይጠቅማል፡፡

ፍትሕ
እኩልነት

ልማት
ዴሞክራሲ

አማራ